# ቶማስ ሳንካራ

## ጥቁሩ አብዮተኛ



"ማማ ሳንካራ ልጆችህ ይበቀላሉ ! "

"ሁላችንም ሳንካራ ነን ! "

"ዘላለማዊ ህይወት ለድሆች ፕሬዚዳንት ! "

በሰሎሞን ዳኜ ቸኮል

# ቶማስ ሳንካራ



## ጥቁሩ አብዮተኛ

ይህን መጽሐፍ ከፀሀፊው ፈቃድ ውጪ በየትኛውም መንገድ ማሰራጨት የተከለከለ ነው።

የአዘጋጁ የቀድሞ ስራ

ለየቅል -ትርጉም (“Things Fall Apart” by Chinua Achebe)

ፀሀፊውን ለማግኘት

ስልክ 0913987763
Email soladagne@gmail.com

https://www.facebook.com/solomon.dagne.7

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ በምእራብ አፍሪካዊቷ ሀገር ቡርኪና ፋሶ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር 1980ዎቹ ላይ እንደ ጠዋት ጮራ ብርሀን ፈንጥቆ በአጭሩ የተቀጨውን ወጣቱን ተራማጅ ፕሬዚደንት ቶማስ ሳንካራን አጭር የፖለቲካ ታሪክ ይዳስሳል። ቶማስ ሳንካራ ምድር ላይ 37 ዓመታትን ብቻ የተራመደ ነገር ግን በማእበል ማየል የማይጠፋ ዱካ አሳርፎ ያለፈ የዘመናችን አፍሪካዊ አብዮተኛ ነው።

በቅኝ ግዛት ወቅት "አፐር ቮልታ" ትባል የነበረችውን በርሀማ ደሀ ሀገሩን "ቡርኪና ፋሶ" ወደሚል ይፋዊ መጠሪያ የቀየረ፣ ተበታትነው ይኖሩ የነበሩት ህዝቦቿ ቡርኪናቤ የተሰኘ የጋራ ማንነት እንዲጋሩ ያደረገ፣ ለዜጎቹ ይህወት የሚገደው ባለራዕይ መሪ ነበር።

ለምእራባውያን ሀያላን ሀገራት ጫና ሳይንበረከክ በታደመባቸው አለማቀፋዊና አፍሪካዊ ስብሰባዎች ላይ ሁሉ አለምን በማናለብኝነት ሲመዘብሩ ከነበሩ ሀገራት መሪዎች ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ሲተናነቅ ያሳለፈ፣ ለጥቁር ህዝቦችና በደል ላጎበጣቸው ምንዱባን ልሳን ሆኖ ያለፈ፣ አለም ከማይረሳቸው አብዮተኞች መካከል ጎልቶ የሚታወስ አፍሪካዊ እንቁ ነው።

"የራስን የተፈጥሮ ሀብት በራስ ጉልበት ማልማት" በሚለው የሀገሩን ህዝብ ባነቃነቀ ዘመቻ ያስመዘገባቸው አስደናቂ ድሎች አፍሪካ የራሷን ተፈጥሯዊ እድገት እንድታድግ ለማይፈልጉት ምዕራባውያን ሀገራት እንደ ስጋት እንዲቆጠር አድርጎታል።

ድሎት ያማያሸንፈው ቆፍጣናው ወጣት ወደ ፕሬዚደንትነት ከመጣ ጊዜ አንስቶ የቅንጦት ኑሮ ኖሮ አያውቅም። ከተራው ህዝብ ጋር የዩኒፎርሙን እጅጌ ከፍ ከፍ አድርጎ ሰሚንቶ የሚያቦካ፣ አካፋና ዶማ አንስቶ ጥቁር ላብ በግንባሩ እስኪንዠቀዠቅ ድረስ ሰርቶ የሚያሰራ፣ ድሆች ያለ ልኬት የሚሳሱለት መሪ ነበር።

አካሄዱ ባስፈራቸው ምእራባውያን መሪዎች እና ስልጣን ባናወዛቸው የቅርብ ጓዶቹ ደባ በአጭር ቢቀጭም ተራማጅ ሀሳቦቹና ያስመዘገባቸው ተጨባጭ ለውጦች ዛሬም ድረስ ስሙ ተደጋግሞ እንዲነሳ አስችለውታል።

# የአዘጋጁ መልዕክት

የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ከአንድ ወጥ ድረሰት የተቀዳ አይደለም። ቶማስ ሳንካራን በቅርብ ከሚያውቅትና በተደጋጋሚ ቃለመጠይቅ ካደረጉለት ጋዜጠኞች መካከል አንዱ በሆነው ኧርነስት ሀርች ተጽፎ በኦሀዮ ዩንቨርሲቲ ፕረስ በ2014 የታተመውን የግል ታሪኩን እንደ ዋና የታሪክ ምሰሶ ተጠቅሜአለሁ። ከዚያ ባሻገር በተለያየ መንገድ ስለ ቶማስ ሳንካራ የተጻፉና በዘጋቢ ፊልም መልክ የተዘጋጁ በዛ ያሉ ማጣቀሻወችን ተጠቅሜ ለአንባብያን ምቹ በሆነና ታሪኩን ሊያጎለብት በሚችል መንገድ ለማዘጋጀት ሞክሪያለሁ።

ብዙ የተበጣጠሱ ሁነቶችን በመገጣጠም ስሜት ሊሰጥ የሚችል ጽሁፍ ለማዘጋጀት የተቻለኝን አድርጊያለሁ። በእኔ አሰሳ ስለ ቶማስ ሳንካራ የተጻፉ መጽሀፍት ኢትዮጵያ ውስጥ ማግኘት አልቻልኩም። በመሆኑም የሰውየውን ምሳሌ ሊሆን የሚችል ታሪክና በተለይ አሁን ሀገራችን ካለችበት የፖለቲካ ሁኔታ አንጻር የዚህ ሰው ታሪክ በተደራጀ መልኩ በመጽሀፍ መልክ መውጣቱ ብዙ ውዥንብሮችን ሊያጠራ ይችላል ብየ በማመኔ በእኔ ፍለጋ የደረስኩባቸውን እውነታዎች፣ መላ ምቶችና ታሪካዊ ሁነቶች አደራጅቼ ለማቅረብ ሞክሪያለሁ።

ወደፊት ይህን መጽሐፍ በመንተራስ ወይም እኔ ካገኘኋቸው የተሻለና የተብራራ መረጃ ማግኘት የሚችሉ ጸሐፍት አስፍተው ሊጽፉት እንደሚችሉ ሙሉ እምነት አለኝ።

መጽሐፉ የሚያተኩረው ፖለቲካዊ ታሪኩ ላይ ስለሆነ በተለይ በግል ሕይወቱ ዙሪያ ያለው መረጃ የተመጠነ ሆኖ ይገኛል።

አንብባቸሁ እንድታዳብሩትና ቀረ የምትሉትን እንድትጨምሩበት እያሳሰብኩ መስተካከል ይገባዋል የምትሉትን ሁሉ ገንቢ በሆነ መንገድ ብታሳውቁኝ ለማረም ዝግጁ ነኝ።

**መልካም ንባብ!**

# ምስጋና

ፈጣሪ ይመስገን ከብዙ መማሰን በኋላ መጽሐፉ ለፍሬ በቅቷል። ስሰንፍ ላበረታችሁኝ፣ ስዘገይ ለጎተጎታችሁኝ፣ ተስፋ ልቆርጥ ሲዳዳኝ ጉልበት ለሆናችሁኝ የስራ ባልደረቦቼና ጓደኞቼ በሙሉ ምስጋናየ ይድረሳችሁ።

በሆሄያት ለቀማ፣ በይዘት ዝግጅት ግምገማና በአጠቃላይ የታሪክ ፍሰትና የቋንቋ አጠቃቀም እርምት ላይ ያለ መሰልቸት ለተሳተፋችሁት ባልደረቦቼና ጓደኞቼ ጋዜጠኛ ጥበቡ ይርዳው፣ አሸናፊ ደምሴ እና ተሾመ ብርሃኑ አክብሮቴ ላቅ ያለ ነው።

የመጽሀፉን ሽፋንና አጠቃላይ ገጹን ያሳመርከው ወዳጄ እምርታ ድሪባ እጅህ ይባረክ።

# በሳንካራ ዘመን

በቅኝ ግዛት ስያሜዋ “አፐር ቮልታ” ትባል የነበረችው

በረሀማዋ ምዕራብ አፍሪካዊት ሀገር “ቡርኪና ፋሶ” የተሰኘ አዲስ ስያሜ ባለቤት ሆነች። ለወትሮው ተበጣጥሰው ይኖሩ የነበሩት ህዝቦቿ ቡርኪናቤ የተሰኘ የጋራ ማንነት ተጋሩ።

ፕሬዚደንቱን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ደሞዛቸውና ጥቅማጥቅማቸው ተቀንሶ ለልማት ዋለ። ሁሉም ቅንጡ መኪኖች ተሸጡ። በድህው ሀብት መንደላቀቅ የህልም እንጀራ ሆነ።

በህዝብ ከፍተኛ ርብርብ በራስ ሀብት፣ በራስ ጉልበት በግርምት እጅን አፍ ላይ የሚያስጭኑ መሰረተ ልማቶች ተገነቡ።

ገበሬው ከከተሜው ተቀናጅቶ የመስኖ ግድቦችን ገነባ። በርሀማ ሀገሩን በአከባቢ ጥበቃ ዘመቻ ጸዳል አለበሰ። በአራት ዓመታት ውስጥ ቡርኪና ፋሶ በምግብ እራሷን ቻለች።

በአፐር ቮልታ ጉዳይ አድራጊ ፈጣሪ የነበረችው ፈረንሳይና አሳባቂዋ አሜሪካ ከወጣቱ መሪ ብርቱ ፈተና ገጠማቸው። የለመዱት መንግስትን እንደፈለጉ የማሽከርከር ልማድ ተኮላሸ።

የወጣቱ አብዮተኛ አካሄድ ፍርሀት ያጫረባቸው ሀያላን ሀገራት ጥርሳቸውን ነከሱበት።




በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113 691933/0118346305

ዋጋ 170 ብር